www.stop-fgm.admin.ch

Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra

**The Federal Council**

# ከሴቶች ግርዛት ጥበቃን የሚገልጽ ደብዳቤ

በስዊዘርላንድ ኮንፌዴሬሽን የተሰጠ የሴት ልጅ



**ናቸው።የተከበራችሁ የቤተሰብ አባላት፣ ክቡራትና ክቡራን**

የስዊዝ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛት በስዊዝ የወንጀል ሕግ መሰረት የሚያስቀጣ መሆኑን ያረጋግጣል። ግርዛቱን የሚፈጽሙትም ሆኑ ይህን ድርጊት የፈጸሙ ወይም አስተዋጽኦ ያደረጉ ወላጆችና ዘመዶች ስዊዘርላንድ ውስጥ ከባድ የሕግ ቅጣት እንደሚጣልባቸው መጠበቅ አለባቸው። ግርዛቱ የተፈጸመው በውጬ ሃገር ቢሆንም፣ ድርጊቱን ፈጻሚው ሰው ስዊዘርላንድ ውስጥ ከሆነ ቅጣቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

ለሴት ልጃችሁና ለመላ ቤተሰባችሁ ጥበቃ ሁኔታ ማክበርና የሴት ልጅ ግርዛት ከመፈጸም መቆጠብ አለባችሁ። በርዕሱ ላይ ተጨማሪ መረጃ እዚህ ሰነድ ውስጥ ታገኛላችሁ።

**Elisabeth Baume-Schneider**
የፌዴራል ምክር ቤት አባል፣ የፌዴራል የአገር ውስጥ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ (EDI)

**Beat Jans**
የፌዴራል ምክር ቤት አባል፣ የፌዴራል ፍትህ እና ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ (EJPD)

### የሴት ልጅ ግርዛት ምንድን ነው?

የሴት ልጅ ግርዛት ማለት ውጫዊ የ የጾታ ብልት ክፍልን በከፊል ወይም በሙሉ መቁረጥ ማለት ነው። የሴት ልጅ ግርዛት ውስጥ የሚካተቱ ሌሎች እንደ ቀላል የሚታዩ ተግባራት፣ ለምሳሌ የሴት ብልትን መብሳት/መተልተል።

# የሴት ልጅ ግርዛት ክልክል ነው

የሴት ልጅ ግርዛት በስዊዘርላንድ እና በሌሎች በርካታ ሃገራት ውስጥ ክልክል ነው።

> የስዊዝ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 124 (StGB): የሴት ልጅን ብልት መቁረጥ
>
> [1] የሴትን የመራቢያ አካላት የቆረጠ፣ ተፈጥሯዊ ተግባራቸውን እንዳይወጡ በከፍተኛ ሁኔታና በዘላቂነት ያደናቀፈ ወይም በሌላ የትኛውም መንገድ ጉዳት ያደረሰባቸው ማንኛውም ሰው ከስድስት ወር እስከ አስር ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።
>
> [2] አንድ ግለሰብ ወንጀሉን የፈጸመው በውጭ ሃገር ሆኖ፣ ስዊዘርላንድ ውስጥ ካለና ወደ ሌላ ሃገር ካልተባረረም በወንጀል ሊከሰስ ይችላል። [...]

የሴት ልጅ ግርዛት ስዊዘርላንድ ውስጥ በወንጀል ያስቀጣል...

**... ድርጊቱ በውጭ ሃገር የተፈጸመ ቢሆንም እንኳን።**

... ድርጊቱ የተፈጸመው „ክሊኒክ" ውስጥ እና/ወይም በጤና ባለሙያ ቢሆንም እንኳን።

... ድርጊቱ የተፈጸመው ወይም የተመቻቸው ወደ ስዊዘርላንድ (ለመጀመሪያ ጊዜ) ከመገባቱ በፊት ቢሆንም እንኳን። ስለዚህ አንዲት ልጅ የትውልድ ሃገሯን ለቅቃ እንድትሄድ በማሰብ ከሆነም የተገረዘችው።

# የሴት ልጅ ግርዛት ያስቀጣል

### ማነው የሚቀጣው?

- የሚቀጡት ግርዛት ፈጻሚዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ሴት ልጃቸውን ያስገረዙ ወላጆችና ዘመዶችም ጭምር ናቸው።
- እናት እና አባት (ወይም እንደሁኔታው ሌሎች አሳዳጊዎች) ሴት ልጃቸውን የመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው። ሴት ልጃቸውን ከግርዛት ካልተከላከሉ፣ እነርሱም ይቀጣሉ።
- የስዊዘርላንድ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ስዊዘርላንድ ውስጥ ከተገኘና ወደ ሌላ ሃገር ተላልፎ ካልተሰጠ (ለምሳሌ፡- ለጉብኝት ወይም ትራንዚት)፣ በወንጀል ተከሶ ሊቀጣ ይችላል።

### ቅጣቱ ምንድን ነው?

- ቅጣቱ ከስድስት ወር  እስከ አስር ዓመት የሚደርስ እስራት ነው (የስዊዝ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 124/1)።
- በተጨማሪም፣ አንድ የውጭ ዜጋ በወንጀሉ ጥፋተኛ ከተባለ ከስዊዘርላንድ ለከ5- እስከ 15 ዓመታትዓመት ይባረራል (አንቀጽ 66a ንኡስ አንቀጽ 1/b StGB)።

# የሴት ልጅ ግርዛት የተከለከለው ለምንድን ነው

የሴት ልጅ ግርዛት በሰለባዎቹ ላይ የዕድሜ ልክ፣ ከባድ አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ማሕበራዊ መዘዞች አሉት። በርካታዎቹ ከድርጊቱ መፈጸም በኋላም ስቃይ ይኖርባቸዋል፤ ለምሳሌ፦ ሕመም፣ ኢንፌክሽን፣ መካንነትና በወሊድ ወቅት የሚከሰቱ ችግሮች። በተጨማሪ፣ የሴት ልጅ ግርዛት በሚፈጸምበት ወቅት በሚኖር የደም መፍሰስ ወይም ኢንፌክሽን ምክንያት ሞት ሊከሰት ይችላል።



**ማወቅ የሚገቡ ጠቃሚ ነጥቦች፦** የሴት ልጅ ግርዛት ወንጀል እና የሰው እና የህጻናት መብት ላይ ከፍተኛ ጥሰት ነው። በሴቶች እና በህፃናት ላይ የሚፈጸም ጥቃት ነው።

## ተጨማሪ መረጃ

የፌዴራል የማሕበረሰብ ጤና ቢሮ
www.stop-fgm.admin.ch

### ምክር

ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ምክር ካስፈለገዎት፣ የስዊዝ ኮንፌዴሬሽን የሚመራዎት ወደ ስዊዘርላንድ የሴት ልጅ ግርዛትን የሚከላከለውን የኔትዎርክ ብሔራዊ ተጠሪ ነው።

ስዊዘርላንድ የሴት ልጅ ግርዛትን የሚቃወም መረብ
www.mekinschab.ch
ኢሜይል፦: mikri@mekinschab.ch
ስልክ ቁጥር፦ +41 41 419 23 55

**ኢምፕሪንት**

አሳታሚ፦ ስዊዝ ኮንፌዴሬሽን
ቀን፦ 01.12.2023

BBL no. 316.203.amh



Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra

**The Federal Council**

የሴት ልጅ ግርዛትን የሚከለክለው የስዊዝ ደብዳቤን የተመለከተ

# ተጨማሪ መረጃ

## ልጅዎትን ከግርዛት ይከላከሉ

ሴት ልጃቸው በውጭ ሃገር ግርዛት ተፈጽሞባት ይሆናል የሚል ስጋት ላለባቸው ወላጆችና ሌሎች ሞግዚቶች የሚሆን ጠቃሚ መረጃ።.

ከቀጣዩ አካል ጋር በመተባበር

Network against female genital cutting Switzerland

### ከጉዞ በፊት፡-

- በዙሪያዎት ካሉ ሰዎችና ከባለሙያዎች ጋር ይነጋገሩ፡- ሴት ልጅዎን ከግርዛት እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ ለመወያየት ከ Network against Female Genital Mutilation Switzerland ጋር ይነጋገሩ። ከሚያምኑት ዶክተር ጋር ይነጋገሩ (ለምሳሌ፡- የሕጻናት ሐኪም፣ የፅንስና ማሕፀን ሐኪም ወይም የቤተሰብ ዶክተር)።
- ከቤተሰብ ጉብኝቶች ይታቀቡ ወይም ለሌላ ጊዜ ያራዝሙ፡- ሴት ልጅዎ መገረዝ አለባት የሚሉ ዘመዶች ካሉዎት፣ በተቻለ መጠን ከእነርሱ ጋር አለመገናኘት ወይም ለጉብኝት ሲሄዱ ሴት ልጅዎን ይዘው መሄድ የለብዎትም።
- ለሴት ልጅዎ ይህን መረጃ ይስጡ፡- ከሴት ልጅዎ ጋር (በዕድሜዋ መሰረት) ስለጤናዋና የሴት ልጅ ግርዛት ስለሚያስከትለው ስጋት፣ ከዚህ ነገር ለምን እንደሚከላከሏትና ምን ዓይነት ባህርይ ማሳየት እንዳለባት ተነጋገሩ።

### በቦታው ላይ፡-

- ወደ ውጭ ሃገር ጉዞ በሚያደርጉበት ወቅት ምንጊዜም የጥበቃ መስጫ ደብዳቤውን መያዝ አለብዎት። ከጉዞ ሰነዶችዎ ጋር አብረው ይያዙት።
- ከሴት ልጅዎ ጋር በቅርበት ይሁኑ ወይም ለረዥም ጊዜ ለዘመዶችዎ አደራ ትተዋት አይሂዱ።
- ሴት ልጅዎን በመጠበቁ ሒደት ሊያግዙዎት የሚችሉ ባል/ሚስት፣ የኑሮ አጋርና ሌሎች ለእርስዎ ቅርብ የሆኑ ሰዎችን ያካትቱ።
- በአሁኑ ጊዜ በውጭ ሃገር የሚገኙ ከሆነ፣ ስዊዘርላንድ የሴት ልጅ ግርዛትን የሚቃወም መረብ የሚባለውን ድርጅት ያነጋግሩ።

### ተጠቃሚ።

**ግርዛት የተፈጸመባት ወይም ግርዛት ሊፈጸምባት የደረሰቻ ልጅ ጥፋቱ የእርሷ ባለመሆኑ የወንጀል ክስ አይመሰረትባትም። የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ልጃገረዶችና ሴቶች ጥበቃና ድጋፍ የማግኘት መብት አላቸው።**

### ጥያቄዎች አሉዎት ወይም ምክር ያስፈልግዎታል?

የ ስዊዘርላንድ የሴት ልጅ ግርዛትን የሚቃወም መረብ ብሔራዊ ተጠሪ

ስልክ ቁጥር፡- +41 41 419 23 55
ኢሜይል፡- mikri@mekinschab.ch
www.mekinschab.ch
Facebook Messenger:
www.facebook.com/femalegenitalcutting

የምክር አገልግሎቶች የሚሰጡት ከክፍያ ነጻ ሲሆን፣ ስምዎት ሳይጠቀስና አስፈላጊም ከሆነ በአስተርጓሚ እገዛ አገልግሎቱ ይሰጣል።

**ለድንገተኛ ጉዳይ፡- ለፖሊስ በስልክ ቁጥር 117 (ስዊዘርላንድ) ወይም 112 (አውሮፓ) ይደውሉ።**

BBL no. 316.203.amh ቀን፡- 01.12.2023